# ለአገር ዘላቂ ጥቅም ማሰብ የአገር ወዳድ መለያ ነው

ክፍል አንድ

*አዲስ ቶልቻ 08/25/13*

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን በሃይማኖት ሽፋን የሚደረገውን እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ በሰጡት መግለጫ መንግሥት በሃይማኖት ሽፋን እየተደረጉ ያሉ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን የታገሰው በቂ ግንዛቤ ሣይኖራቸው በሕገወጥ ድርጊት የሚሣተፉ ወገኖች ከድርጊቱ እንዲርቁ እድል ለመስጠት እንደሆነ አስታውሰዋል፡፡

መንግስት ሃይማኖታዊ ተልእኮ ሣይኖራቸው በሃይማኖት ሽፋን የሚንቀሳቀሱትን ተከታይ ግለሰቦች የመለየት ፅኑ እምነት ስለነበረው ሕገወጥ እንቅስቃሴውን በትእግስት ሲከታተል መቆየቱን፣ እንቅስቃሴው ሃይማኖታዊ ሽፋን በመላበሱ ጽንፈኞችን ከሃይማኖተኞች የመለየቱ ሂደት ጊዜ መውሰዱንም አስታውቀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር አያይዘውም፤ በሃይማኖት ሽፋን ድብቅ አጀንዳቸውን የሚያራምዱ ኃይሎች ኢ-ህገመንግስታዊ ከሆነው ድርጊታቸው እንደቆጠቡ ከጽንፈኞች ጋር ተቀናጅተው የአገሪቱን ሠላም ለማወክ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማስጠንቀቂያ አዘል ማሣሰቢያ ሰጥተዋል፡፡

ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማሣሠቢያ ሦስት ነገሮችን ይዟል፡፡ አንድ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መኖሩን፣ ሁለት እንቅስቃሴው ሃይማኖታዊ መስሏቸው በየዋህነት ቡድኑን የተቀላቀሉ ሰዎች መኖራቸውን፣ ሦስት ሕጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃይማኖትን ሽፋን ካደረጉ ጽንፈኞች ጋር ተቀናጅተው የሃገሪቱን ሠላም ለማወክ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

እነዚህን ሦስት ሃሳቦች አንድ በአንድ እንመልከታቸው፡፡ ሃይማኖትን ሽፋን ካደረገው የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንጀምር፡፡ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ሁለት አስርት አመታት አስቆጥሯል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የሃይማኖት መብትና ነፃነት ጥያቄን መነሻ ያደረገ ያለመሆኑን በቀደሚነት የሚያሣየው በእነዚህ ሁለት አስርት አመታት በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሃይማኖት መብትና ነፃነት በሕገመንግስት የተረጋገጠባቸውና ይህ በተግባርም የታየባቸው አመታት መሆናቸው ነው፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 27 "የሃይማኖት የእምነትና የአመለካከት ነፃነት" በሚል ርእስ ሥር "ማንኛውም ሰው የማሰብ የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፤ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል ይላል፡፡ በንኡስ አንቀፅ 3 ላይ ደግሞ "ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡" ይላል

ከነዚህ መሠረታዊ የሃይማኖትና የእምነት መብትና ነፃነት ድንጋጌዎች በሕገመንግስቱ ላይ ሠፍረው የቀሩ አይደሉም፡፡ በተግባርም ተረጋግጠዋል፡፡ አንድም ኢትዮጵያዊ ሙስሊም፣ ክርስቲያን ወይም ዋቄፈታ "እነዚህ የሃይማኖትና የእምነት መብትና ነፃነቶቼ ተደፍረውብኛል፡፡" አይልም፡፡ ይህ ሕገመንግሥታዊ የሃይማኖት መብትና ነፃነት በሕገመንግሥት በተረጋገጠባቸው ያለፉ አመታት በተለይ ቀደም ባሉት የመንግስት ስርዓቶች ጫና በየመንደሩ ከነበሩ መድረሳዎች ያለፈ፣ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች በስፋት የመሠራጨት እድሉ ቀጭጮ የነበረው የእሥልምና ሃይማኖት ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃት ታይቷል፡፡

በአገሪቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚስማማበት ከላይ በተገለጸው አኳኋን የሃይማኖት መብትና ነፃነት በመረጋገጡ፣ የሃይማኖት መብትና ነፃነት፣ እኩልነት ጥያቄ የለም፡፡ የእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ ሊነሣበት የሚችል ምንም አይነት ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ባይኖርም፣ በሕገመንግስቱ በተረጋገጠው የዕምነትና የአምልኮ ነፃነቶች ውጭ የሆኑ ሃይማኖተኞ ነን በሚሉ ሰዎች የሚመሩ እንቅስቃሴዎች ግን ታይተዋል፡፡

ባለፉት ሃያ አመታት በተለያዩ ወቅቶች በአርሲ፣ በባሌ፣ በወሎ፣ በሃረርጌ አካባቢዎች ነባሩ የአሕለል ሱና የኢትዮጵያ እስልምና አስተምህሮ ታሪካዊ የእምነት ሥፍራዎችና መስጊዶች ተቃጥለዋል፡፡ በኢትዮጵያ እስልምናን በማስፋፋታቸውና በሃይማኖታዊ ስብእናቸው ስመጥር የነበሩ የእስልምና ሃይማኖት አባቶችና መሪዎች መቃብራቸው ተቆፍሮ አፅማቸው ተጥሏል፡፡ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች የልጅ ልጆቻቸው በሚሆኑ ወጣቶች በአደባባይ ተዘልፈው እንዲሸማቀቁ ተደርጓል፡፡ ተደብድበዋል፣ በመጥረቢያ፣ በገጀራ፣ በጥይት አረር ተደብድበው ሕይወታቸው አልፏል፡፡ እነዚህ የሃይማኖት አባቶች የሚያሳተምሩባቸውና የሚመሩዋቸው መስጊዶች ውስጥ በሌሊት ተሸሽገው የገቡ ጋጠወጥ የሰለፊ ወሃቢ ጀሌ ጎረምሶች ተፀዳድተውበቸዋል፡፡

በ1999 ዓ/ም ለግጭት መነሻ የሚሆን ሰበብ በመፈለግ በጅማና በኢሊባቦር የተወሰኑ ወረዳዎች ከሃዋርጂያ ተባለ የዋሃቢ ሠለፊ ቡድን ክርስቲያኖችን በግድ እናሰልማለን በሚል በርካታ ክርስቲያኖች፣ ሕፃናቶችና አዛውንቶችን ጨምሮ በአሠቃቂ ሁኔታ ጨፍጭፈዋል፡፡ በተመሣሣይ በ2003 ዓ/ም በጅማ ዞን አሞ ናዳ ወረዳ አሠንዳቦ ከተማና አካባቢው ሃሠተኛ ሰበብ በማዘጋጀት የፕርቴስታንት ክርሲቲያኖች የመኖሪያ ቤቶችና ቤተእምነቶች በእሣት ጋይተዋል፡፡

ቡሣ ሠገል የተባለ የዋሃቢ ሠለፊ ቡድን ሃሠን ጃርሶ በሚባል ኬንያዊ መሪነት የጀሃድ ጦርነት ለማወጅ ባሌ አካባቢ ሲንቀሣቀስ ነበር፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በአልቃይዳ ወደ አገር ውስጥ በተላከ አማን አሠፉ የተባለ ግለሰብ ሃረከቱል ሸበብል ፊ ቢላል ሂጅራይተን የተባለ የወሃቢ ሠለፊ የጀሃድ ቡዱን በደቡብ ወሎ አካባቢ ሲንቀሳቀስ ነበር፡፡

እንግዲሕ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ የሃይማኖት እኩልነት በተረጋገጠባቸው ባለፉ ሁለት አስርት አመታት በአገሪቱ የተቀሰቀሱ በተለይ የእስልምና ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ እንቅስቃሴዎች መነሻና መድረሻ የሃይማኖት መብትና ነፃነት እኩልነት ጥያቄ መይደለም፡፡ ማንም ሊከደው በማይችለው ሁኔታ የሃይማኖት መብትና ነፃነት በመከበሩ፡፡

ከአንድ አመት በፊት በአዲስ አበባ አወሊያ መስጊዱ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ተሰብስበው "የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ" በሚል የሰየሙት፣ በኋላም በሃገር ውስጥና በውጭ "ድምፃችን ይሠማ" በሚል በሕቡእ የሚንቀሳቀሰውም ቡድን ዓላማና መድረሻ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን የመብትና ነፃነት ጥያቄ አይደለም፡፡

"ድምፃችን ይሠማ" ከሚለው ሕቡዕ ቡድን ጀምሮ ሁሉም ሃይማኖትን የታከኩ እንቅስቃሴዎች መነሻቸውና መድረሻቸው የሃይማኖት መብትና ነፃነትን፣ እኩልነትን ማሰከበረ ሳይሆን፣ ከውጭ የገባን ወሃቢ ሰለፊ የተሰኘ የአክራሪነት አስተምህሮን እንደአመለካከት ከሌሎች አመለካከቶችና እመነቶች ሁሉ የበላይ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ የዚህ አስተምህሮ መሰረቱ ሳኡዲ አረቢያ ነው፡፡

የዋሀቢ ሰለፊ የእስልምና አስተምህሮ ተከታዮች ፣ እንደማንኛውም ሃይማኖት ወይም የሃይማኖት ክንፍ ሕገ መንግስታችን በሚሀቅደው መሰረት ተከታዮች ማፍራትና ከሌሎች ሃይማኖቶችና እምነቶች ጋር በእኩልነት የመንቀሳቀሰ መብት ያላቸው መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ችግሩ የወሃቢ ሰለፊ አስተምህሮ ከማንኛውም የሃይማኖትና ሌሎች አመለካከቶች የበላይ መሆን አለበት የሚል አቋም ያላቸውና ይህን ተግባራዊ ለማድረገ በፔትሮ ዶላር የሚደገፉ መሆናቸው ላይ ነው፡፡ ይህ ሕገመንግስታዊ መሰረት የለውም፡፡

የወሃቢ ሰለፊ እንቅስቃሴ ጳላማ አስተምህሮውን እንደርዕዮተ አለም (እንደአመለካከት) የበላይ ማድረግና ሁሉም ሰዎች በዚህ የሃይማኖት አስተምህሮ ሥር እንዲኖሩ ማዱረግ ነው፡፡ ይህ የበላይነት በምኞት ብቻ እንደማይሣካ ግልፅ ነው፡፡ ከሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች ምድራዊ አመለካከቶች ሁሉ የበላይ ይሆን ዘንድ አራማጆች የመንግስት ሥልጣን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን አመለካከት የበላይ ለማድረግ የሚካሄደውን እስልምናን ሽፋን ያደረገ እንቅስቃሴ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ይህ ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የወሀቢ ሠለፊ አስተምህሮ የተፈጠረው እ ኤ አ ከ1703 እስከ 1792 ዓ/ም በኖረው መሃመድ ኢብን አብድ አልዋሃብ በተባለ የሃይማኖት መምህር በአሁኑ ሣኡድ አረቢያ ነው፡፡ ይህ አስተምህሮ በሣሙዲ አረቢያ የመንግሥት አይዲዮሎጂ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፤ አሁንም በማገልገል ላየ ይገኛል፡፡

ሣሙዲ አረቢያ እ ኤ አ በ1970ዎቹ ከነዳጅ ንግድ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ስትጀምር ሁሉም ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው አገራት ርዕዮተ ዓለማቸውን ወደተቀሩት የዓለም አገራት በማስፋፋት በእነርሱ አምሣል የተቀረፁ አገራት (satellaite countries) ለመፍጠር እንደሚንቀሳቀሱት ሁሉ፣ ሣኡዲ አረቢያም እንደርዕዮተ አለም የምትመራበትን የዋሀቢ ሠለፊ የእስልምና አስተምህሮ ወደሌሎች አገራት በተለይ የእስልምና ተከታይ ወደ ሆኑ የአለም አገራት የማስፋፋት ዘመቻ ጀመረች፡፡

ለዚህ አላማም በእስላማዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አማካኝነት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር መመደብ ጀመረች፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ብቻ ሣሙዲ አረቢያ የዋሃቢ ሠለፊ አስተምህሮን ለማስፋፋት 87 ቢሊዮን ዶላር መመደቧን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህን የወሃቢ ሠለፊ አስተምህሮ በገንዘብ የመደገፍ ተግባር ከሣሙዲ አረቢያም አልፎ በነዳጅ ንግድ የከበሩ ሌሎቸ እስላማዊ የአረብ ሃገራትም ተቀላቅለውታል፡፡ ይህ የዋሃቢ ሠለፊ አመለካከት እንደርእዮተ ዓለም ወደሌሎች የማዛመት ዘመቻ መድረሻ በተለይ የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ አገራት እስላማዊ መንግሥት መመስረት ነው፡፡ ዘመቻው በሠላዊ መንገድ ብቻ ሣይሆን በኃይልም (በጀሃድ) የሚከናወን ነው፡፡

የአውሮፓ ፓርላማ በቅርቡ ይፋ ባደረገው ሪፖርት የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ሥር ወሃቢ ሠለፊ መሆኑን ደርሼበታለሁ ብሏል፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ ውጭ ያሉ የዋሃቢ ሠለፊ ቡድኖችም በመላው አለም ለሚገኙ እስላማዊ አማፂ ኃይሎች የጦር መሣሪያ እርዳታ እንደሚያደርጉ

ያስታወቀው የአውሮፓ ፓርላማ ሪፖርት፣ “አማጺ ቡድኖቹ የሚቃወሙዋቸው ላይ የሽብር ጥቃት ስለሚፈፅሙ ደጋፊዎቻቸው ደግሞ ስለሚያደንቁና ስለሚያሞካሹ ማንኛውም እስላማዊ አገር ከእንቅስቃሴያቸው የፀዳ ሊሆን አይችልም፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶቻቸው የተለያየ ነባር እስልምና አስተምሮ ተከታዮች የነበሩባቸው የእስልምና ተከታዮች የሚኖሩባቸው አገራት የዋሃቢ ሠለፊ አስተምሕሮን እንድቀበሉ እያስገደዱ ነው፡፡ የበጎአድራጎት ድርጅቶቹ ትስስር ሙስሊም ወዳልሆኑ የአውሮፓ የሰሜን አሜሪካ አገራት በመዛመት በተመሳሳይ ሁኔታ  የስጋት ምንጭ ሆነዋል፡፡” ይላል ፡፡

እንግዲህ በተለያየ ወቅትና ስያሜ ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱት እስልምናን ሽፋን ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ከላይ የተገለጸው የዋሃቢ ሠለፊ አስተምህሮን በሽብር ጥቃት በሌሎች ላይ በመጫን በመጨረሻም በዚህ አስተምህሮ የሚመራ እስላማዊ መንግስትን የመመስረት ዘመቻ አካል ነው፡፡ እንቅስቃሴውን ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርገው ይህ ነው፡፡

ሁለተኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በንግግራቸው ውስጥ የገለፁት ሃሣብ “እንቅስቃሴው ሃይማኖታዊ መስሏቸው በየዋህነት ቡድኑን የተቀላቀሉ ሰዎች አሉ” የሚለው ነው፡፡ ይህ በተለይ በሣኡዲአረቢያ የዋሃቢ ሠለፊ በጎአድራጎት ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ የአስተምህሮው ማዕከል ሆኖ ሲንቀሳቀስ በቆየው የአወሊያ መስጊድ “ የሙስሊሙ መፍትሄ ፈአላጊ”  በኋላም  “ ድምፃችን ይሠማ” በሚል ቡድን ሥር ያሉትን ይመለከታል፡፡

በአወሊያ መስጊድ የተጀመረው እንቅስቃሴ በሁለትና በሦስት አስርት አመታት ውስጥ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት በቅድሚያ አወሊያ ተቋምን በዋሃቢ ሰለፊ አሰተምህሮ ማዕከልነት ማቆየት እንዳለበት አቋም ይዟል፡፡ በመቀጠልየኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤትን የመቆጣጠር እቅድ ነው የነበረው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የአወሊያ ቡድን እንቅስቃሴውን የጀመረው የእስልምና ሃይማኖት ተወካይ ኢተዮጵያዊያን በሕገመንግስቱ ያገኙትን የሃይማኖቶችና የእምነት ነፃነትና እኩልነት እንዳልተጣሰ የሚታወቅ ቢሆንም፣ “የሙስሊሙን ጥያቄዎች አንስቼያለሁ” በሚል ነበር፡፡  “የሙስሊሙ ጥያቄዎች” በሚል ላነሳቸው ጥያቄዎች በራሱ በሙስሊሙ መፍትሔ ቢበጅም የተሰጠው መፍትሔ እስላማዊ መንግስት ወደመመስረት እርምጃው ለመግባት ስላልተመቸው ወደሁከት ነው የዘለቀው፡፡

ሁከት ለመቀስቀስ እንዲያግዙት በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸውን ለጋ ወጣቶች አሰባስቦ "መንግስት በሃይማኖታቸሁ ውስጥ ጣልቃ ገብቷል፡፡" በማለት መቀስቀስ ጀመረ፡፡ "መንግሰት አሕባሽ የተሰኘ አስተምህሮ አምጥቶ በግዳጅ እየሰጠ ነው" የሚለውን ወሬ በማናፈስ መንግስት "በሃይማኖትህ ጣልቃ ገብቷል" በማለት የተጠቀመበት መቀስቀሻ ውሸት መሆኑ በኡላማዎች ምክር ቤት ተረጋገጠ፡፡

ቡድኑ ይህን አካሄዱን ትቶ ባይተወውም ብዙም እንደማያዘልቅ ስለተረዳ "የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ከመስጊድ ውጭ በቀበሌ እንዲካሄድ ተደርጓል" የሚለው ላይ አተኮረ፡፡ በተለይ በወጭ አገራት የሚኖሩት ድምጻችን ይሰማ የሚሉና ሌሎች ቡድኑን ለራሳቸው የፖለቲካ ዓላማ መጠቀም የሚፈልጉ ተቃዋሚዎች ይህን ጉዳይ ማብጠልጠልን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል፡፡ 8 ሚሊየን ገደማ በሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ተመርጦ የተሰየመውን የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የሚቃወሙትም ይህን ሰበብ በማድረግ ነው፡፡

የአክራሪው ቡድን ጀሌዎች ከዚህም አልፈው መንግስትንና መንግስታዊ ተቋማትን እንዲዘልፉ፣ ሕገወጥ የመንግሥት ለውጥ እንቅስቃሴ እንዲያሚሙቁ፣ በአክራሪው ቡድን የተወሰዱ ግድያን የመሰሉ ሕገወጥ እርምጃዎች ተጠያቂ አጥተው እንዲድበሰበሱ ከአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተቀናጅተው የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ በመሣሪያነት እያገለገሉ ነው፡፡

ለአንድ አመት ያህል በአዲስ አበባ ታላቁ አንዋር መስጊድ፣ አልፎ አልፎም በበኒ መስጊድ ሰላማዊ የጸሎት ስርአትን ከሚያውኩ ወጣቶች ጀርባ የሚነዳቸው የፖለቲካ ዓላማ ያለው የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪ ቡድን ነው፡፡ ብዙዎቹ የሁከት ጀሌ የሆኑት አፍላ ወጣቶች ከጀርባቸው ያለውን የሚነዳቸውን ኃይል የመረዳት ብቃት የሌላቸው ናቸው፡፡ እንቅስቃሴውን የተቀላቀሉትም ተረድተውት ሳይሆን ተደናግረው በስሜታዊነት ነው፡፡

የፖለቲካ ዓላማ ያለውን የወሃቢ ሠለፊ አክራሪ ቡድን ከድርጊቱ እንዲታቀብ የሚወሰድ እርምጃ እነዚህን በአክራሪው ቡድን ቅስቀሳ ሳያወቁ በስሜት እየተነዱ የተቀላቀሉ ወጣቶችን አብሮ እንዳይጨፈልቅ ጥንቃቤ መደረግ ነበረበት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "መንግስት እስከዛሬ አክራሪውን ቡድን በትዕግስት የጠበቀው በቂ ግንዛቤ ሣይኖራቸው በሕገወጥ ድርጊት የተሣተፉ ወገኖችን ከድርጊቱ እንዲርቁ ዕድል ለመስጠት ነው" ያሉት የዋሆችን ከአጥፊው ጋር ላለመጨፍለቅ የተደረገውን ጥንቃቄ ለመግለፅ ነው፡፡ በክፍል ሁለት ፅሁፍ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም በሰጡት ማሳሰቢያ የአክራሪዎቹንና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጥምረት በተመለከተ ያነሱትን ሶስተኛውን ሃሳብ እንመለከታለን፡፡